# ያልተንኳኩ በሮች

## መንፈሳዊ መጣጥፎች

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ባፕቲስት ቤተክርስቲያን
Ethiopian Evangelical
Baptist Church
2822 S. Jupiter Rd.
Garland, TX 75041
Tel: (214) 703-0100 Fax: (214) 703-0161
WWW.EEBC-DALLAS.ORG

ጳውሎስ ፈቃዱ

አሳታሚ ጳውሎስ ፈቃዱ

ግንቦት ፳፻ ዓ.ም የመጀመሪያ እትም
ጥቅምት ፳፻ወ፩ ዓ.ም ተሻሽሎ 2ኛ ታተመ
ሐምሌ ፳፻ወ፩ ዓ.ም 3ኛ እትም

ይህንን መጽሐፍ በከፊልም ይሁን በሙሉ በማንኛውም ዐይነት መንገድ ለማባዛት በቅድሚያ ከጸሓፊው ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል::

Copyright© 2008 Paulos Fekadu

P.O.Box 1614
Addis Ababa
Ethiopia

E-mail: paulosvictory@yahoo.com

በዚህ መጽሐፍ ከሚገኙት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች፦
አ.መ.ት የሚለው በ1993 ዓ.ም ከታተመው አዲሱ መደበኛ ትርጉም፣
አዲስ ትርጉም የሚለው ቀለል ባለ አማርኛ ተተርጉሞ በ1997 ዓ.ም ታርሞ ከታተመው አዲስ ትርጉም፣
ሕያው ቃል የሚለው በ1998 እ.ኤ.አ ከታተመው አዲስ ኪዳን ሲሆን፣
የቀሩት በሙሉ ከድሮው (1954 ዓ.ም) መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ናቸው::

የሽፋን ሥዕል ልዑል ገብርኤል

የኮምፒዩተር ጽሑፍ ይሳኮር ቢዝነስ ሴንተር 091-1636319

በእግዚአብሔር ዕረፍት ለምትኖረው
እናቴ~
አባይነሽ ሥዩም (አቡ)

## ውዳሴሆሙ

ስለ ሁሉም እግዚኦ እሴብሐከ!

ይህ መጽሐፍ የተለያዩ መንፈሳዊ መጣጥፎች ስብስብ ነው። መጣጥፎቹም ለጌታ በመኖርና እርሱን በማገልገል፣ በፍቅርና በጋብቻ እንዲሁም በሌሎች የሕይወት እንጓዎች ላይ ያተኩራሉ። አንዳንዶቹ ያስቃሉ፤ ሌሎቹ ደግሞ ያስቆጣሉ፤ ያስገርማሉ፤ ያጽናናሉ። በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረቱ ናቸውና መንፈሳዊ ቁምነገር እንደሚያስተምሩ ተስፋ አደርጋለሁ። ዋነኛ አጀንዳቸው በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ትስስርና መስተጋብር በመሆኑም የተበታተኑ አይደሉም፤ በማይበጠስ ክር ተሰፍተዋል! ከ1992 ዓ.ም እስከ 2000 ዓ.ም ከተጻፉት ከእነዚህ መጣጥፎች መካከል፣ ነባሮቹ በተለያዩ መጽሔቶችና ጋዜጦች ላይ ታትመዋል። ሆኖም ከሌሎቹ ጋር ተጣጥመው እንዲኖሩ ሲባል አሁን ትንሽ ተቀባብተዋል። አዳዲሶቹን ግን የሰውም ዐይን አላያቸው!

መጻፌን ሳስብ የእናት አባቴ የተጽዕኖ ድርሻ ከፍተኛ መሆኑን እቀበላለሁ። አባቴ በማለዳ ዐልጋው ላይ ሳለ ማንበብ ይጀምራል (አቤት የእናቴ ትዕግሥት!)። የዕለቱ የመጨረሻ ሥራውም ማንበብ ነው፤ እንቅልፍ እስኪጥለው ያነብባል። ደብዳቤ እንኳን ለመጻፍ ብዕርን ከወረቀት ሲያዋድድ አይቼው ባላውቅም የማንበብ፣ ዕውቀትን የመከተል፣ ለእውነት ዋጋ የመስጠትና የድፍረት ምሳሌዬ ነው።

እናቴ ግን ከማንበብ ጋር ብቻ ሳይሆን ከጽሑፍ ጋርም ቤተኛ ናት። በተለይ የአገሪቱ ዋነኛ ሥራ በሚመስለው የስብሰባ ባቡር ስትሳፈር ግጥም መጻፏ የማይቀር ነው። እስልቺ ካድሬ ሲያጋጥማትማ ማታ የሚነበብልን ግጥም በሽበሽ ነው። ተረትና ምሳሌ የግሏ ነው። በመምህርነቷም ሲሆን ይችላል፤ ነገርን ከሥሩ ማስረዳት ተክናበታለች።

እነዚህ ሁለት ሰዎች ሲደመሩ (ወይም ሲባዙ) እኔ ተገኘሁ። ታዲያ ከዚህ ውጭ ምን መሆን እችል ነበር? ስለዚህ እናትና አባቴ ተለያይተው ማየት የማልሻውን ያህል፣ ጸሐፊነትና አንባቢነት ተፋትተው መመልከትንም እጠላለሁ።

መጣጥፎቹን አሰማምቼ በአንድ ጉጆ ውስጥ እንዳኖርና በዚህ መልክ እንዳሳትም ሲጐተጉቱኝ የነበሩ ሰዎች ጥቂቶች አይደሉም፤ ሆኖም ቶሎ እጅ አልሰጠኋቸውም! የሦስት የማይታከቱ ሰዎች ግፊት ግን በስተመጨረሻ ሐሳቤን አስቀይሮኛል። እያንዳንዱን ነጠላ ጽሑፌን ከየትናየት መጥቶ እያነበበ መሄስ የማይታክተው የዳዊት ጸጋዬ (አዳምና ሔዋን) መዋጮ ዘርፈ ብዙ ነው። ጽሑፎቼ ጥንካሬያቸውን ጠብቀው እንዲቀጥሉ አድርጓል። ይህንን መጽሐፍ፣ እንደ ምግብ "በያይነቱ"



ወይም "ማኅበራዊ" በማለት እንዳልሰይመው የገላገለኝም እርሱ ነው። ለእኔ ልጅ እርሱ ስም አውጥቷል! ከነሚስቱ አመሰግነዋለሁ። ስለ ወይንሸት እባተ የማውቀው እንደምትጸልይልኝ ብቻ ነው። እስካሁን አይቻት ባላውቅም በቀጭኑ ሽቦ በኩል አሸንፋኛለች። የሽመልስ ኀይሌ ምክር ግን ንዝነዛ ሊያስብል የሚችል ጥንካሬ ነበረው።

ወደ ኅትመት ከመሄዴ በፊት የአርትኦት ሥራ የሠሩልኝ ሰዎችም አሉ። የዘወትር ወዳጄ ደረጀ በላይነህ የመጀመሪያው ሲሆን፣ ርኅራኄ በማያውቀው አስተያየቱ አሰልቺ ድግግሞሾቼን ሲቀናንስ ነበር።

የበቀለ ወ/ኪዳን (መጋቢ) በሳል ጥቆማም ከጉድ አውጥቶኛል። መጽሐፉን አንብቦ የጨረሰበት ፍጥነትም "ጋሽ በቄ" ዕድሜን ለሽፋን ብቻ የሚጠቀምበት አስመስሎታል።

ዘማሪ ገዛኸኝ ሙሴ በነገረ መለኮትና ሥነ ጽሑፍ ዕውቀቱ ጉድለቶቼን ነቅሶ እያወጣ አስተካክሏል። መብራት በፈረቃ በሚጠፋበትም ጊዜ በሻማ ሳይቀር ያነብ ስለነበር የስጠሁትን ጥራዝ በሻማ ነጠብጣብ ቢያበላሽብኝም በይቅርታ ዐልፌዋለሁ።

የሥራ ባልደረባዬ ሥዩም በሻህ ከቅርበቱ የተነሣ ያላለቁ ሥራዎቼን ከሥር ከሥር የማየት "ዕድል" ነበረው። ሁልጊዜም ጥያቄው የሚዛናዊነት በመሆኑ፣ ጽሑፎቼ ሚዛናዊ ሆነው ከተገኙ ምስጋናው የእርሱ ነው። ካልሆነ ግን ጥቆማውን ባለመቀበሌ ነው።

የወሰድኳቸውን ሐሳቦች በተቻለኝ መጠን ምንጫቸውን ለመጠቆም ሞክሬያለሁ። ሳልጠቅስ ያለፍኳቸው ይኖሩ እንደሁ እንጃ! ዋቢ መጻሕፍትን ማሰባሰብ በቀላሉ ለብቻ የሚከውኑት ሥራ አለመሆኑን ግን አሁን ነው የተረዳሁት። እኔ የማላገኛቸውን አንዳንድ ማመሳከሪያዎች ምንተስኖት ተሾመ፣ ሙሉቷ አብጤና ዮሴፍ አሌ በየበኩላቸው አግኝተውልኛል።

እያንዳንዱን ጽሑፍ ሳዘጋጅ አኩያ እኅቴ ሰላም ጠይቃ፣ አብሮ ዐደር (room mate) ታናሽ እኅቴ ፍቅር ደግሞ ተጠይቃ ያነበቡና አርምት ካለ ይነግሩኛል። ከነድካሜ ስለሚያውቁኝ ላታልላቸው አልችልም። ብቻ የልፋታቸውን ዋጋ በገንዘብ እንዳይጠይቁኝ ነው ሥጋቴ!

የእኔና የቤተሰቤ ወዳጅ የሆነው በላይ ተሰፋዬ የጭን ኮምፒውተሩን አውሶኝ፣ ጥንቃቄ የሚፈልገውን አሰልቺ የመጨረሻ የአርማት ሥራ በሄድኩበት ሁሉ እንድሠራ አስችሎኛል።

እንደተለመደው የሽፋን ሥዕሉን የሠራልኝ ሠዓሊ ልዑል ገብርኤል ነው! እኔ እኔን ባልሆን ኖሮ ይህንን መጽሐፍ ለሽፋኑ ስል እንደምገዛው ጥርጥር የለኝም። አሁን አሁንማ ከልዑል ተሰጥኦም ይሁን ተቀብዬ ላይ ርስት እንዳለኝ ማሰብ ጀምሬያለሁ። የናፈቀኝ፣ የሚቀጥለውን መጽሐፍ ሽፋን መቼ እንደሚሠራልኝ ነው!

በእነዚህ ደጋግ ሰዎች ትከሻ ላይ ተንጠላጥዬ ባገኘሁት ተጨማሪ ቁመት ከፊት ይልቅ አሁን ዕይታዬ ጠርቷል። በብዙ ወዳጆች ለመከበቤ ጌታን እመሰግናለሁ። "ዘመደ ብዙ ጠላው ቀጭን ነው" ቢባልም፣ መጽሐፉ ግን ሲወፍርለት ይችላል።

ጽሑፎቹ መጽሔት ላይ ስወጡ ቁጥር ሥራዬ ብለው አስተያየት ሲሰጡኝ የነበሩ በቁጥር በርከት ያሉ ወገኖችም ከምስጋናው ላይ ድርሻቸውን መውሰድ መብታቸው መሆኑን ይወቁት

የትኛውም ሰው እንከን የለሽ መጽሐፍ ሲጽፍ አይችልም፤ ለዚህ ነው በዚህ ምድር ላይ ከመጽሐፍ ቅዱስ በቀር ትክክለኛና ፍጹም መጽሐፍ የሌለው። ይህኛውም መጽሐፍ ቢሆን ከዚህ የተለየ ባለመሆኑ ሁለተኛ ሲታተም መሻሻል አስፈልጎታል። በተለይ ሚኪያስ በላይ፣ ስሜታደሰ (መጋቢ) እና ተስፋሁን ሐጢያ ለዚህ ተመስጋኞች ናቸው። መሻሻል አለባቸው ያሏቸውን ጉዳዮች ለማመልከት መጽሐፌን በቀይና በአረንጓዴ እስኪሪብቶ አዥጎርጉረውና ሥዕል ደብተር አስመስለው ሰጥተውኛል። "Vive La Différence!" ይላሉ ፈረንሳዮች፤ "(የአሳብ) ልዩነት ለዘላለም ይኑር!" ማለታቸው ነው። እኔስ ምኔ ሞኝ ነው? ያመንኩበትን ብቻ መርጬ ተቀብያለሁ። ቅንነታቸውን አደንቃለሁ። በሆዴ ግን፣ "ብድር መላሽ ያድርገኝ!" እያልኩ ነው።

በተረፈ ባለማወቅ ለማቸውን ያልጠቀስኳቸው ሰዎች ቢኖሩ የዝንጋኤ ጉዳይ መሆኑን ተረድተው ይቅርታቸውን እንደማይነፍጉኝ ባለ ተስፋ ነኝ።

እኔ ባጎደልኩ ሥላሴ ይሞሉበት!

አሁን እኔ ላብቃና መጽሐፉና እናንተ ቀጥሉ።

ጳውሎስ ፈቃዱ

ሚያዝያ 30 ቀን 2000 የምሕረት ዓመት

አዲስ አበባ



## "እግዚአብሔርን አልወደውም"

ልጅቷ ብስል ቀይ ናት - ቆንጆዬ። ማግባት የምትፈልገው ደግሞ እንደ እኔ ድብን ያለ ጥቁር ወንድ ነው። ከጠረፍ አካባቢ የሚመጡት ጥቋቁርና ዝግባ የሚያካክሉ ወንዶች ይማርኳታል - በልቧም ትመኛቸዋለች። ግና የእህል ውሃ ነገር ሆነና መልኩ መለስ ካለ ሰው ጋር ተገናኝተው ፍቅር ይጀምራሉ። ጥቁር ለሆነ ወንድ ያላትን ከፍተኛ ፍላጎት የተረዳው ፍቅረኛዋ (አሁን ባሏ ሆኗል)፣ "ምናለ ፀሐይ ላይ ብሰጣላትና ብጠቁር!" ብሎ መመኘቱን አስታውሳለሁ። ሰዎች ፍቅር ሲይዛቸው ያፈቀሩት ሰው እንደሚፈልገው ራሳቸውን ለውጠው ፍቅረኛቸውን ለማስደሰትም ሆነ ለማሸነፍ ይሞክራሉ - ከሆነላቸው መልካም። ለዚህ ነው "ጀንትል" ወንድ የምትወድ ሴት ያዘዘበት፣ "ጀንትል" ለመሆን በመሞከር የሚለፋው። ተጫዋች የምትፈልግ ያጋጠመችውም ቀልጣፋና ተጫዋች ለመሆን ደፋ ቀና ሲል ይውላል፤ ሌላውም እንዲሁ የተለወጠውን ራሱን ለሚወዳት ሴት ለማቅረብ ሲዳክር ይታያል።

እግዚአብሔርን ስለ መውደድም ስናነሣ ስለ ፍቅር ነው የምናወራው። ፍቅር ደግሞ ንድፈ ሐሳብ ብቻ ሳይሆን ተግባር፣ ስውር ሳይሆን ግልጥ ነው።

ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት የጀመረው እርሱ አስቀድሞ ሲወደንና ፍቅሩን በመሥዋዕትነት (በተግባር) ሲገልጥልን ነው። ሲወደን ደግሞ በምድራዊ ፍቅር ብዙ ጊዜ እንደሚስተዋለው ፍቅሩ ጊዜያዊ አልነበረም፤ "የወደዳቸውን እስከ መጨረሻ ወደዳቸው" (ዮሐ. 13÷1) ይላል መጽሐፉ[1]። ፍቅር ደግሞ ሰጥቶ የመቀበል ጉዳይ ነውና የሁለቱንም ተሳትፎ ይጠይቃል። በአንድ እጅ ማጨብጨብ እንደማይቻል ሁሉ በፍቅርም ጉዳይ እንዲሁ ነው። የሁለቱም ወገኖች ፍላጎትና መሥዋዕትነት ያስፈልጋል። እግዚአብሔርን ጨምሮ የትኛውም አፍቃሪ ለፍቅሩ ምላሽ ይሻል። ስለዚህ እርሱ እንደ ወደደን በምላሹ እኛም እርሱን መውደድ ይጠበቅብናል።

"እግዚአብሔርን አልወደውም" ብዬ ስናገር ሰዎች ሲሰሙ፣ "እንዴ ትወደዋለህ እንጂ!" ብለው ይከራከራሉ። "እንዴት ሰወቃችሁ?" ብዬ ብጠይቅ፣ "እንዲህና እንዲያ አድርጎልሃል እኮ" ይሉኛል። ማስረጃቸው ግን እርሱ እንደሚወደኝ እንጂ እኔ እንደምወደው አያረጋግጥም። ታዲያ ሰዎች ጌታን መውደዱን በምንድን ነው የሚያውቁት? ቤተ ክርስቲያን ስለምሄድ? ዐሥራት በመስጠቴ? ወይስ በአገልግሎቴ?

ይዘምራሉ፤ እግዚአብሔርን ግን በፍጹም አይወዱትም!! ይልቁን ራሳቸውን ያስቀድማሉ፤ ገንዘብን ያመልካሉ፤ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን ይወዳሉ። ስለዚህ አውነት እውነት እላችኋለሁ፤ ውሸተኞች ናቸው!

የምራቸውን እግዚአብሔርን ከልባቸው እየወደዱ ትእዛዙን መፈጸም ያቃታቸውን ግን እግዚአብሔር ይርዳቸው!

ማስታወሻ

[4] በነገራችን ላይ በዓለም ላይ "መጽሐፉ" (The Book) የሚባለው መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው። ይህም እቻ የለሽ የመሆኑ ማስረጃ ነው።



# "ሴ*ን እንደማላገባ"

ርእሱን ያየ ባለትዳር የሥራ ባልደረባዬ፣ "ወይ ጉድ! ለምን እንደማታገባ ማወቅ ቀርቶ እግብተህ እንኳን ለምን እንዳገባህ ማወቅ አትችልም" ብሎኛል። ቢሆንም ሰዎች የማያገቡባቸው የየራሳቸው ሰበቦች ይኖራቸዋል ብዬ አገምታለሁ። ስለዚህ አንዳንድ ወዳጆቼን ለምን እስከ አሁን ሴጣ እንደሆኑ ላቀረብኩላቸው ጥያቄዎች የሰጡኝን ምላሽ እንደሚከተለው አቅርቤዋለሁ። በእርግጥ ጥያቄዎቹ በሙሉ ወንዶች ላይ ያነጣጠሩ ናቸው። ምክንያቱም ሴቷን ልጅ፣ "ለምን አታገቢም?" ብዬ ብጠይቃት፣ "ለምን አታገቢኝም?" ያልኳት መስሏት ችግር እንዳይፈጠርብኝ ሠግቼ ነው። ስለዚህ የሴቶቹን ጉዳይ ራሳቸው ሴቶቹ እንደሚያስቡበት ተስፋ በማድረግ የእኛኑ ጣጣ ልቀጥል። ለነገሩማ፣ "የወንዶች ጉዳይ" የሴቶችም አይደል እንዴ?

አንዱን ጠየቅሁት፤ "አንተ ግን ለምንድን ነው የማታገባው?"

"አንተ ራስህ ለምን አታገባም?" ጥያቄዬን አንጥሮ መለሰው። "የማትኖርበትንማ አትሰብከኝም!" አለኝ እያሾፈ።

"እኔ እኮ 'አግባ' እያልኩ ልዘበዝብህ አይደለም። ምክንያቱን ለማወቅ ስለምፈልግ ብቻ ነው የጠየቅሁህ" በማለት በዐይኔ ጭምር ተለማመጥኩት።

"ለምን እንደማላገባ ልንገርህ?" አለኝ፤ አንቁልልጭ የሚል ይመስላል።

"አዎን!" አልኩት በጉጉት።

"ከየት ላምጣ?" አለኝ ፍርጥም ብሎ።

"ምን!" አልኩት በድንጋጤ።

"ሚስት ነዋ!" ሲለኝ ልቤ መለስ አለ። ሁሉ የሞላው ቀጭን ጌታ በመሆኑ አንዳች ኢኮኖሚያዊ ችግር እንደሌለበት ዐውቃለሁ።

"እንዴት አንተ ሚስት ታጣለህ?" ጥያቄዬን ገፋሁበት።

"ወንድም! የልጆች የሰንበት ትምህርት ቤት (sunday school) ዘትጊደ እንኳ ሚስት አታገኝም። የ12 እና 13 ዓመት ልጆች እጮኛ አላቸው። ጴንጤ እኮ ስግብግብ ሆኗል። የቀሩት ገና ያልተወለዱት ብቻ

"መጀመሪያ ከገነት አባረሩን፤ አሁንስ ታዲያ የት እንሂድላቸው?" የሚሉ አንዳንድ ሰዎች አጋጥመውኛል:: "አልሰሜን ግባ በለው!":: ወደንና ፈቅደን ልባችን እያወቀ ጭምር የወሰንነው ውሳኔ ነው እንጂ እነርሱ እኮ መቼም አታልለውን አያውቁም:: "የተታለለም አዳም አይደለም" ይለናል መጽሐፉ (1ጢሞ. 2÷14)::

ሔዋን መጀመሪያ ፍሬውን ራሷ በልታ፣ ለአዳምም ይዛለት የመጣችው ተቀብሏት እንደሚበላ በማወቋ ነው (እነርሱ የሰጡንን ሁሉ እንበላለና!):: አዳም፣ "የለም አልበላም" ብሎ እግዚአብሔርን ቢመርጥ፣ ሔዋንን ሲያጣ ሆነ:: "እሺ" ብሎ ቢበላ ደግሞ ከሚስቱ ጋር መኖር ይችላል፤ ከእግዚአብሔር ጋር ግን ሲጣላ ነው:: ታዲያ ከሔዋን ጋር ሆኖ እግዚአብሔርን ከማጣትና ከእግዚአብሔር ጋር ሆኖ ሔዋንዬን ከማጣት የቱ ይሻላል? አዳም ያለ ሔዋን ኖሮ ያውቃል፤ ትዝታው እንኳን ያንገፈግፋል:: ስለዚህ አሁን እነዚያ ዘግናኝ ቀናት ተመልሰው እንዲመጡበት አልፈለገም (በስመአብ!):: ያለ እግዚአብሔር ግን ኖሮ አያውቅም:: ታዲያ ቢሞክረውስ? ስለዚህ አዳም ከሔዋን በፊት ከሚያውቀው እግዚአብሔር ይልቅ፣ ከእግዚአብሔር በኋላ የሚያውቃት ሔዋንን መረጠ፤ ከሰጭው ይልቅ ስጦታውን አስቀደመ:: እርሱ በደንብ አሰቦበት የወሰደውን እርምጃ እኛም ዛሬ እየደገምነው ነው::

✡ ✡ ✡

በጥፊ የነደደ ጉንጩን እያሻሸሁ የትምህርት ቤቱን ደረጃ የወረድኩት ይህን ሁሉ እያሰብኩ ነበር:: ሆኖም ሴቶች የዚህ "የወንዶች ዓለም" ፈርጦች መሆናቸውን አልክድም (በመገሳ ካልዘጋሁ ጉዴ ነው፤ ሩቅ እንኳ ሳልሄድ እንትዬ መርዝ ነው የሚሰጡኝ!):: ሴቶች በሌሉበት በተዋበ ገነት ከመኖር፣ ከእነርሱ ጋር ከገነት መባረርን መምረጥ የዘራችን ነው:: በተደራጀ ከተማ ያለ እነርሱ ከመኖር በሰሃራ በረሃ ከእነርሱ ጋር መኖርን መሞከር ይሻላል:: ሣቃቸውም ሆነ ልቅሶአቸው የትኛውንም የሕይወት ልቃቂት የመተርተር ዐቅም አለው:: እነርሱ በተገኙበት ቦታ ሕይወትና ውበት አብረው ይገኛሉ::

"ያለ ሴቶች ተሳትፎ፣ አብዮቱ ግቡን አይመታም!" የምትለዋን የደርግ መፈክር አስታወሳችሁ? ይህንን የሰማ፣ "እንኳን አብዮቱ፣ እይናጋም ሴሲቱ!" ማለቱ ይነገራል:: የእኔም ምኞት አንድ ነው - ገዢዎቻችንን ያኑርልን!

ማስታወሻ

[1] ደረጀ በላይነህ፤ የሰዶማዊ መንገድ (አዲስ አበባ፤ 1997) ገጽ 8::

[2] Oxford Advanced Learner's Dictionary. Sixth Edition. Oxford, Oxford University Press. 2000.



# መጋቢዎቻችንን ማነው የሚመግባቸው?

ጥቂር አሜሪካዊው ምርጥ ተዋናይ ዊል ስሚዝ የተወነበትን "Enemy of the State" የተሰኘ ፊልም አይቼ ነበር:: የፊልሙ ጭብጥ የጸጥታ ሠራተኞች ጉዳይ እንደ ነበር በደንብ አስታውሳለሁ:: የጸጥታ ሠራተኞች ጥፋት ሲያጠፉ ለማነው የምንጮኸው? ሃይ የሚላቸውስ ማነው? "Who keeps the keepers?" የሚለው ነበር የፊልሙ ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ:: "ጠባቂዎቻችንን ማነው የሚጠብቃቸው?" በእውነት መሠረታዊ ጥያቄ ነው:: ጥሎብን በየዕለቱ የምንሰማውን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ነገረ ሥራ በሚመለከት ደግሞ እኔም፣ "ለመሆኑ መጋቢዎቻችንን ማነው የሚመግባቸው?" እላለሁ::

ሕግ አስከባሪ ሕግ ከማስከበሩ በፊት ራሱ ሕጉን አክባሪ መሆን እንዳለበት እሙን ነው:: በእርግጥ በኢትዮጵያ ይህንን መጠበቅ ቅንጦት ይመስል ይሆናል:: የወንጌል አስተማሪዎቻችን አስቀድመው ከእግዚአብሔር የተማሩ እንዲሆኑ መፈለግ ግን በምንም መልኩ ስህተት አይሆንም:: አሊያ ግን ለባኪው፣ "ይቺ ያልጸዳች አጽጂ" እንዳለው መሆኑ ነው:: "ሳይማር ያስተማረንን ኅብረተሰብ ..." ምናምን የምትል በቀደመው መንግሥት የምትደጋገም መፈክር ቢጤ እንደ ነበረችን ታስታውሳላችሁ አይደል? በአንዳንድ መምህራን ብቃት አልባነት የተበሳጨ አንድ ወዳጃችን ደግሞ ትምህርቱን ጨርሶ ሲመረቅ በምረቃ መጽሔቱ ላይ ከፎቶው ሥር፣ "ሳይማሩ ያስተማሩኝን መምህራን አመሰግናለሁ" ብሎ ለመጻፍ ፈልጐ እንደነበረ ትዝ ሲለኝ ፈገግ እላለሁ:: ታዲያ አስተማሪዎቻችን ምን እንደ ተማሩ፣ መጋቢዎቻችን ምን እንደ ተመገቡ ወይም ማን እንደሚመግባቸው ለማወቅ ብንጠይቅ ምናለበት?

ይህን ጥያቄ ለማንሣት የምደፍረው ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ትልቅ አክብሮት ስላለኝ ነው:: አባትን ማክበር የልጅ ድርሻ መሆኑን አቀበላለሁ:: አባቴን እወደዋለሁ፣ አከብረዋለሁ ማለት ግን የሚያደርገውን ነገር ሁሉ ትክክል ነው ብዬ እቀበላለሁ ማለት አይደለም:: ለእርሱ ያለኝ አክብሮት እርሱ ሲሳሳትና የነገረኝ ከሚያደርገው ጋር ሲለያይ "ልክ አይደለህም" ብዬ እንዳልሞግተው አያደርገኝም:: በዚያው ልክ ደግሞ አክብሮቴንም አይቀንስብኝም:: ስለዚህ ዛሬ መሪዎቻችንን የምጠይቀው በዚህ መንፈስ ሆኜ ነው፤ በአክብሮት:: ወላጆችም ቢሆኑ ልጆቻቸው አድገው አሠራራቸውን ሲጠይቁ በመብቃታቸው መደሰት ይገባቸዋል::

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዛሬ እዚህ ለመድረስ ብዙ ዋጋ እንደ ከፈሉ ከማንም የተሰወረ አይደለም:: ወንጌል ያለ መከራ አይሆንምና

ጉዳይ በተግባር የተደገፈ ትምህርት ለጥቶአል። አሁን መሪዎቻችን ዘንድ እያየን ያለነው ግን አገልጋይ መሪነትን ሳይሆን ጌትነትን ነው፤ መጋቢዎቻችን ጌቶች ሆነውብናል። ሕዝቡንም ወደ ክርስቶስ ከማመልከት ይልቅ እነርሱን እንዲመለከት አድርገውታል።

የአፍሪካ መሪዎችና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መጋቢዎች ከአንድ እናት የተወለዱ ወንድማማቾች ይመስሉኛል። በሥልጣንና በክብር ጉዳይ ቀልድ አያውቁም። ከመዋሸትም አይመለሱም። ታዲያ ጌታ በየት በኩል ይታይ?

በዚህ ሁሉ መሐል ግን ጾምና ጸሎት ይታወጃል፤ የንስሐ ፕሮግራምም ይዘጋጃል። ጾም ጸሎቱንና ንስሓውን ራሳቸው መሪዎቹ አስቀድመው የሚያደርጉት ከሆነ መልካም ነው። ራሱን ያላቀና ሌላውን አያቀናማ! ይህ እንኳ ቢቀር በጾምና በጸሎት በጌታ ፊት ከሕዝቡ ጋር አብረው ቢወድቁ በተሻለ! ሆኖም እነርሱ ያበላሻሉ፤ ሕዝቡ እንደ ፈረደበት ቀንበሩን ይሸከማል፤ የእነርሱ ስህተት የሚወራረደው በምዕመኑ የንስሓ እንባ ይመስል!

ይህን ስል ግን በእግዚአብሔር ፊት በፍርሀትና በመንቀጥቀጥ የሚራመዱ፣ ከሕዝቡ ቀድመው ሁሌ በጌታ ፊት የሚወድቁ ጠንቃቃ መሪዎች የሉም ለማለት አይደለም። አባቶቻችን እንደሚሉት፣ "ክፍል ያመለጡ ባቄላዎች" ዛሬም አሉ። ስለዚህ ምክንያታዊነት የጐደለው ጥቅል ድምዳሜ (hesty generslization) አይዳዳኝም። ነቢዩ ኤልያስ፣ "ብቻዬን ቀርቻለሁ" ሲል እግዚአብሔር ሰባት ሺ ሰዎች ነበሩት (1ነገ. 19፥10፤ 14፤ 18)። አሁንም ከእነዚህ የሚበዙ ሊኖሩ ይችላሉ፤ በሰው ባይታወቁም።

ስጊዜው ማውራት የምፈልገው ግን በሌላ ጐን ስለሚገኙት ነው። ሕዝቡ ንስሓ ይገባል፤ ይጮኻል፤ እነርሱ ግን ከእቋማቸው ንቅንቅ አይሉም (ፍንክች የአባ ቢላዋ ልጅ!)። ልባቸው ያላመነበት ንስሓ ታዲያ ለምን ያስፈልጋል? እንዲህ ዐይነቶቹን ሰዎች እግዚአብሔር፣ "እነሆ፤ በጾማችሁ ቀን ፈቃዳችሁን ታደርጋላችሁ" ነው የሚላቸው (ኢሳ. 58፥3)።

ሌላው ጉልህ ችግር ደግሞ የሌላውን ራእይ አለመቀበል ነው። አንዳንድ አገልጋዮች የተለየ ራእይ ኖሯቸው መሪዎች ባርከው እንደ ሸኟቸው ዐልፎ ዐልፎ እንሰማለን (ከስንት አንዴ!)። እንዲህ ዐይነት ቅንና በጐ አሳቢ መጋቢዎች መኖራቸው ያስደንቃል። ታዲያ ይህ የጥቂቶች ሳይሆን የሁሉም መጋቢዎች መገለጫ መሆን ያለበት ነው። በአብዛኛው ግን፣ "የተለየ ራእይ አለኝ" የሚል ካለ ይነቀፋል፤ ይወገዛል፤ ሰዎችም ወደ እርሱ እንዳይሄዱ ይመከራሉ። ጨክኖ ከወጣና በተለይም ስኬታማ ከሆነ ደግሞ ዳግመኛ ወደ "ቤተ ክርስቲያናቸው" ለአገልግሎት አይጋበዝም። የመዘምራን፣ የወጣቶችና የተለያዩ አገልግሎት አለቆችም በዚያ



ሰው ጸጋ መጠቀም እንደማይችሉ ተጠርተው ይነገራቸዋል። ከእርሱ ጋር የታየም ጥቁር መዝገብ ላይ ስሙ ይሰፍራል።

እያንዳንዱ አገልጋይ ራሱን ችሎና ደቀ መዝሙር ሆኖ ጌታ በጠራው ጥሪና በሰጠው ጸጋ መሠረት መሥራቱ መልካም መሆኑ አይጠፋቸውም፤ ተግባራቸው ግን ተቃራኒ ነው። እስቲ ይታያችሁ፣ የራሳችሁ ሥራም ሆነ ትዳር ሳይኖራችሁ ሁልጊዜ እርሱን ስታገለግሉ እንድትኖሩ የሚፈልግ አባት ቢኖራችሁ ምን ትላላችሁ? ስህተቱ አንድ ይመስለኛል፤ ትልቁን ሥዕል - የክርስቶስን አካል - አንዲቷን ቤተ ክርስቲያን ማየት አለመቻላቸው! (They are majoring in minors!) ስለዚህም ትኩረታቸው ለጕጣቸው ብቻ ሆነ።

ይህ ነገር ሥር የሰደደ መሆኑን የምረዳው ደግሞ መጋቢዎቻችን ምዕመኑ እንዲያነብ መምራት፣ ማበረታታትና ምሳሌ መሆን ሲኖርባቸው ጭራሹኑ የማያነቡ በመሆናቸው ነው። ስህተታቸውን የሚነግራቸው ጽሑፍማ "በቤተ ክርስቲያናቸው (ቤተ መንግሥታቸው)" ቅጥር ግቢ እንዲገባ አይፈቀድለትም (ይህ ጽሑፍም ደጃፋቸውን ማለፍ ከቻለ ከታምራት ይቆጠራል)።

አንድ መጋቢ ያደረገውን ልንገራችሁ፤ አሳፋሪ ስህተቱ በአንድ መንፈሳዊ ጋዜጣ ተዘግቦበት ስለነበረ ጋዜጣውን በብዛት ገዝቶ ሰብስቦና እሳት ለኮሰበት! መቼም ጋዜጣ ሰብስቦ ያነደደ አንጀቱ ያረረ ፓስተር የጋዜጣውን አዘጋጅ ፊት ለፊት ቢያገኘው ምን እንደሚያደርገው እናንተው ገምቱ! ሲግመንድ ፍሮይድ (Sigmond Freud) ትውስ አለኝ።[1] ናዚዎች መጽሐፎቹን ሰብስበው በሕዝብ ፊት ሲያነድዱበት፣ "ጥሩ ለውጥ ነው ያመጣነው፤ መቼም በመካከለኛው ዘመን ቢሆን ኖሮ እኔኑ ነበር የሚያነዱኝ። አሁን ግን መጽሐፎቼን በማንደድ ብቻ ረክተዋል" ብሎ ነበር የተናገረው። "What progress we are making. In the Middle Ages they would have burned me. Now they are content with burning my books." ሰዎች የሚቃጠሉበት ዘመን ማለፉ መልካም ነው። የማይደግፈንን ጽሑፍ ለማስወገድ ስንል፣ መንግሥት በሕግ ያስወገደውን ሳንሱር ሕይወት ልንዘራበት መሞከራችን ግን ያስተዛዝባል።

አለማንበባቸውና ዕውቀት የጐደላቸው (ዕውቀትን የሚጠሉ) መሆናቸው ዋናው ሰበብ-ድርጊት ይመስለኛል። በዚህ ላይ ደግሞ የሚያውቅ ሰው ሲገኝም ፊት ይነሱታል። ስለዚህ ስለ እግዚአብሔር የሚያስተላልፉት ዕውቀትም ጤነኛ አይደለም። በአንድ የራብ ዘመን የነቢያት ልጆች ሲርባቸው አንዱ ወደ ሜዳ ወጥቶ የለበሰበውን ምናምንቴ ነገር ሁሉ በወጡ ምንቸት ውስጥ ጨመረው፤ ምግብ ይሆን ዘንድ። ሰዎቹ ግን ገና እንደ ቀመሱት፣ "በምንቸቱ ውስጥ ሞት አለ!" ብለው ጮኹ እንጂ ሊበሉት አልቻሉም (2 ነገ. 4፥38-40)። ዛሬም ሙሉ ካልሆነው ስሁታቸው የሚወጣው ትምህርት ሞት አለበትና ተከታዮቻቸው ስለ

## ፍቅር ምናባቱ!

ወታደሩ በጀግንነቱ የታወቀ ነውና ትልቅም ይሁን ትንሽ የማይ ሳተፍበት ጦርነት የለም:: ስለዚህ በማለዳ ተነሥቶ የጦር ልብሱን እየለባ በሰ ነው:: የሚፈልጋቸው ትጥቆች፣ ስንቁም ጭምር በሚገባ ተሟልተ ውለታል:: ጠላቱን ገና በሩቅ የሚያይበት አቅርቦ መመልከቻ መነጽሩን አስቀድሞ ነው የያዘው:: ስለ ጠላቱ የውጊያ ዕቅድና ምሽግምሙሉ መረጃ አለው:: ወደ ፍልሚያው ስፍራ ሲደርስ ግን እንዲትም ጥይት ሳይተኩስ ተማረከ:: ለካ ያ ሁሉ ዝግጅት ለምርኮኝነትና ለእስረኝነት ነበር:: ፍቅርም ልክ እንደዚህ ነው፤ ለማሸነፍ ሳይሆን፣ እጅ ለመስጠት የምንታጠቅበትና የምንሰማራበት ጦርነት!

ፍቅር እንደ ሕልምም ነው:: አንዳንዶች ሕይወታቸውን ሙሉ ይህንን ሕልም አያልሙም፤ የተረጋጋች ነፍስ አለቻቸው:: ሌሎች ሕል ሙን ሲያዩ ዐድረው ሕልማቸውን ጨርሰው ተረጋግተው ይነቃሉ:: ስለ ዚህ በሕልም ዓለም የፍቅር ገነት ይኖራሉ፤ እነኚህም እናት እባት የመ ረቃቸው ናቸው:: ሌሎች ግን ሕልሙን ጀምረው በቅጡ ሳያጣጥሙት በአስደንጋጭ ነገር ባንነው ይነቃሉ:: ተመልሰው በመተኛት ሕልሙን እንዳይጨርሱና በሰላም እንዳይኖሩ ማን ዕድል ይሰጣቸው? አይቻልም፤ በውኑ ዓለምም ተረጋግተው እንዳይኖሩ በዚያ ባላለቀ ሕልም ተመርዘ ዋል:: ያላወቁት እርግማን ይኖርባቸው ይሆን?

ስለዚህ መስከን ከየት ይምጣ? ፍቅር ደግሞ ያቁነጠንጣልና ያፈ ቀረ ሐሳቡ በእንድ አይረጋም:: ቅድም ሌላ፣ አሁን ደግሞ ሌላ ነው:: ቀልቡም አይሰበሰብም፤ ተለዋዋጭ ነው:: የሰውን ነፍስ እንደ ፍቅር የሚያንቀዠቅዥ ሌላ ነገር ይኖር ይሆን? በምንም ዐይነት የዕድሜ ክልል ቢገኝ እንኳ እፍቃሪ፣ "the young and the restless" መሆኑ አይቀ ርም:: እንደ ሕፃንም ይቃጣዋል፤ በትንሽ ነገር ደስ ብሎት ይፈነጥዛል፤ ወዲያው ደግሞ ኩርፍ ይላል:: የቸገረ ነገር!

እያንዳንዱ ሰው ሲወለድ የተጻፈለት የሕይወት መስመር መኖሩን የሚናገሩ ሰዎች አሉ:: ጥቂቶችን ደግሞ ለብዙዎች መፍትሔና መንገድ ይሆኑ ዘንድ እግዚእብሔር ፈጥሯቸዋል:: ሆኖም በሰላም እንዳይኖሩና ዐላማቸውን ከግብ እንዳያደርሱ ፍቅር የሚባል ጣጣ ተፈጠ ረ:: ስለዚህ በፍቅር ጦስ ብዙ ታላላቅ ሰዎች እንዳይሆኑ ሆነው ቀርተ ዋል:: ለመፍ ትሔ የተጠራው ራሱ መፍትሔ ፍለጋ ይጮኻል:: ባለመድኃኒቱም ራሱን ማዳን አቅቶታል::

ፍቅር ጋ ሲደርስ የውሳኔና የማስተዳደር ብቃት ገደል ይገባል:: የትኛውም ውሳኔ ፍቅር አጠገብ ሳይደርስ በሩቁ ነው መፈታት የሚጀ



ምረው:: ብዙ ጠላቶችን ለማሸነፍ የሚበቃ ጉልበት ይህንን ጣጣ ለመቋ ቋም በመውተርተር ይባክናል:: ዐቅም ጨርቅ ይሆናል:: ፍቅርን ከማሸ ነፍ በእውነተኛው ጦር ሜዳ ፈንጂ ላይ እየቆሙ ከሞት ጋር መተናነቅ እፎይታ አለው:: ሳምሶን ትዝ ይለኛል:: ከመንገድ የተጠለፈ፣ የጉልበቱ ብርታትና የጦር ልምዱ ያልጠቀመው ምርኮኛ! ዕለት ዕለት እየደከመ ነበር የሚሄደው:: ዛሬ ሁሉም ደሊላን መርገም ይወዳል:: ግን ተጠያቂ ማነው? ደሊላ ናት መረገም ያለባት ወይስ ፍቅር የሚባለው መርገምት?

ፍቅር እንደ ምስጥ ጉልበትን እንክት አድርጐ ነው የሚበላው:: መቼም ፍቅር አይሸነፍም እንጂ ቢሸነፍ ኖሮ አሸናፊው በርካታ ነገሮችን የሚያከናውንበት በቂ ዐቅም በተረፈው ነበር:: ሲያሻው እንደ ሳምሶን የአ ንድን ከተማ ቅጥር መዝጊያ ነቅሎ በመሸከም ተራራ መውጣት ይች ላል:: ልማር ካሰም ያለመታከት በዲግሪ ላይ ዲግሪ መጨመር ለእርሱ ቀላል ነው:: በግሪኮቹ ሐተታ-ተፈጥሮ (mythology) ላይ እንዳለው አት ላስ ዓለምን በትከሻው ቢሸከምም አያስገርምም:: እንዴ! እንደ ፍቅር ጉል በትን የሚበዘብዝ የታለና?!

አንድ ወቅት "ፍቅር ባለበት ሰላም አለ:: ሰላም ባለበት ..." እያለ የሚዘረዝር ጥቅስ እዚህም እዚያም ተለጣጥፎ ይታይ ነበር:: ግን ምላሽ ያጣ ፍቅር ባለበት ሰላም እንዴት ነው ሲኖር የሚችለው? እዚህ ጋ ሰላምና ፍቅር ጠላቶች ናቸው:: እንዱ ሲመጣ ሌላኛው ድራሹ ይጠ ፋል:: ሕልማቸውን ሳይጨርሱ የደነገጡና የነቁ ሰዎች ባሉበት ሰላም ይታሰባል? ፍቅርን መጉረስና ማጣጣም ጀምረው ሳለ የያዙትን ጉርሻ አጃቸውን ተመትተው የጣሉ ሰዎች መካከል ሰላም ምን ያደርጋል? ባይ ሆን ሰቀቀንን ፈልጉ እንጂ!

መንገዱን አብረው መጓዝ ጀምረው አውላላው ሜዳ ላይ ድን ገት ራሳቸውን ለብቻ ያገኙ ሰዎችማ ሰላም እይኖራቸውም! የሣቅና የደ ስታ ጥላ እንኳ ሳይኖር፣ ሰላም ተገኘ ቢባል ማን ያምናል? እነዚህ አሳ ረኞች ያለባቸውንስ ጣጣ ማን ያውቅላቸዋል? ፍቅርን እንዳይረግሙት፣ ለጥቂት ጊዜም ቢሆን ፍቅርን ቀምሰዋል:: ከወፎቹ ጋር ስለ ፍቅር አዚ መዋል:: ከጨረቃ ጋር ምስጢር አውርተዋል:: ሐይቁ ዳር ከቄጠማዎቹ ጋር በነፋስ ደንሰዋል:: ግና ወፎቹ ድንገት መዘመር አቆሙ:: ጨረቃም ተሰወረች:: ፍቅርን እንዳያሞጋግሱት ደግሞ ሰላማቸውና ዕረፍታቸው ጠፍቶአል:: ባሕሩ ደፍርሷል:: የማዕበሱ ጩኸት ከነጉድ ጓዱ ጋር ተዳምሮ ከሩቅ ያስፈራል:: የተባረኩበት የመሰላቸው ቀን ለጭ ንቅና ለምጥ የታጨበት ሆኖአል፤ የሚወለድ ልጅ የሌለበት ምጥ!

ሰዎች ግን ዛሬም ፍቅርን ይመኛሉ:: ስለ ፍቅር ይዘመራል፤ ይሰበካል:: ጀግናውን ፈሪ ለሚያደርግ፣ ንቁውንና ጉበዙን ለሚያፈዝ ክፉ ባላጋራ ቅኔ ይዘረፍለታል:: ድሮ የሰላም እንቅልፍ የነበረው ሰው ዛሬ ለአፍታ ለማሸለብ ራሱን እጅግ ማድከም ይጠበቅበታል:: በአጁ የያዘው

